# ቁጭ ብሎ ባገኘው

የጉንፋን መድሃኒት ፤ ሞልቶ ከጊቢዬ
አላላውስ ሲለኝ ፤ ተጭኖኝ ከላዬ
እንዴት እያመመኝ ፤ እሞታለሁ ሰዬ ።

ገብረን  አልቀረ ፤ መሞት መታሰሩ
እንዴት አፈቀሩን ፤ አጥር እያጠሩ?
ለምን አንሰለች፤  ዘወትር ገብሩ ።

የማናውቀው አይደል ፤ መች ሆነና እንግዳ
ብልሹ እቃ ወስደን ፤ አንሆንም ባለ እዳ
የወደቀ አንስተን ፤ ወልጋዳ ገዳዳ ።

ትላንትናም ዛሬም ፤ ምንም አልተሰራ
ዘወትር መባዘን ፤ በስቃይ መከራ
ኑሮም አልተገፋ ፤ ጭንቅ ሆነ መራራ ።

ዘመኑ ሆነና ፤ የበዳይ ቀማኛ
ፍርድ ተዛባብን ፤ አልበጀንም ለኛ
በየነ ተባለ ፤ ፍርደገምድል ዳኛ ።

መለስ ብዬ ዛሬም ፤ ቤቴን ስጎበኘው
ልደቱን ሊያከብር ፤ ሰዉን እያሞኘው
ድግሱን ጀምሯል ፤ አልሄደም ብመኘው
አንጀቴ ደበነ ፤ ቁጭ ብሎ ባገኘው ።

ታዛቢው … April 22, 2010